# ከጥንት ሰዐሊዎች[±]

ከጥንት ሰዐሊዋች ከምናውቃቸው
ፍሬ ጽዮን እና ተ/ማሪያም ቀዳሚ ናቸው
በደጋ እስጢፋኖስ ይገኝ ስዕላቸው
ታወቁ በኛ በየሰራቸው በየስማቸው።

ያ ታላቁ ገ/ክርስቶስ
ስዕሉ ረቂቅ ልክ እንደ መንፈስ
ተማሪው የነበር ተስፋዬ ተሰማ
ፈለግ ተከትሎ ስዕሉ የተስማማ
ታወቀ ባንዴ በየከተማ።

አፈወርቅ ተከሌ ከሁሉም ልቆ
ሊቀ ሰዐሊ ውጤቱ ደምቆ
አቻ ደበላ በዲጂታል ስራው
እጅግ ባለም ተደናቂ ነው።

ሌላው ታላቁ እስክንድር በጎሲያን
ስሟን ሲያስጠራ ውድ ኢትዮጵያን
የሱ ተማሪ ወሰኔ ኮርሶፍን
ማን ይዘነጋል ስዕለ መልዕክቱን
ስዕላቱን ቀርጾ በፊደላችን፤

ታልቁ አድባር አለ ፈለገ ሰላም¥
ስራ ውጤቱ ዝንት አይረሳም
ዘርይሁን የትም ጌታ
ካሳ ወ/አገነሁ ገ/ክ/ ሰለሞን
እነዚህ ሁላ ኢትዮጵያውያን
አያኮሩም ወይ ጠቅላላ ወገን።

በዘመናችን በህያውና በሰላሳዎቹ
የማይረሱት ታላላቆቹ
ብርሀኑ ይመኑ ሰልሞን በላቸው
አለሙ ሀ/ማሪያም ወንድሙ ወንዴ
ምን አለ ዛሬ ብትታዩ አንዴ

ከዕንስት ሰአሊ ጫፍ የደረሰች
ማርታ ነሲቡ አማትረሳ ነች
ዛሬም በይወት እፓሪስ አለች
አገሯን ባለም እያሳወቀች።

ተጠርተው አያልቁ እጅግ ብዙ ናቸው
ሌሎች ብዙዎች የማናውቃችው
ብራና ፍቀው ታሪክ ያቆዩ
ባለውለታ ዕጹብ ድንቅ ናችው
አገሬ ፍጹም እንዳትረሳቸው።

ሌሎች በዕደ ጥበበ የረቀቃችሁ
ጥቅማችሁ ብዙ ለናት አገራችሁ
ሳተዘነጉ ዛሬ እናስታውሳችሁ።

ሌላ ምን ይኋል
እንደ ሸብሩ ቤቱ ይቁጠረው
ለማስታወሻ ይህ ጀማሪ ነው።

ክንፈ ሚካኤል
ህዳር ፩ቀን ፳፻፩ ዓ/ም

---

± ከስር የተዘረዘሩት ሰዐሊዎች በሙሉ የተገኙት የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ሎስ አንግለስ ከሚያሳትመው አፍሪካን አርትስ ከሚለው መጽሔት ከተለያዩ ቅጾች እና ቁጥሮች ነው።
¥ ከላይ የተጠቀሰው መጽሔት ውስጥ ሳይሆን ከግሌ ማስታወሻ ነው።